## ገቢር ሶስት

### የአክስት ምክር ይሰማል

የአክስትየው ምክር ሁኔታ በተለይም የሰዎች ኮድ ትክክለኛው በቪዲዮው ውስጥ ተካትቷል፡፡

ኒና - አክስቴ ከአዳማ ጋር መሄዴ ነው

አክስት - እ!

ኒና - ለምን ሁልጊዜ ችግር ብቻ ይታይሻል?

አክስት - አክስት እኮ ነኝ ኒና! እርግጥ ነው ከአንቺ በእድሜ ብዙም ላልበልጥ እችላለሁ ግን እመኚኝ ከእኔ የበለጠ ሕይወት አላየሽም

- ታውቂያለሽ! ወንድ ማለት ትርጉሙ አዳኝ ወይም ሊበላ የተዘጋጀ ማለት ነው፡፡ ከንዱ ላይ አንዴ ከአረፍሽና በጣቱ መሃል ከገባሽ በቃ ጨዋታው ሳይጀመር ተጠናቀቀ ይባላል::አዳማ አለምን እሰጥሻለው ሊልሽም ይችላል ::

ካሪዔ - ኒና ወዲህ ነይ እንጂ፡፡

አክስት - ቤተሰቦቹ ሃብታም ስለሆኑ ያለውን ሊሰጥሽ ቃል ሊገባልሽ ይችላል ስጦታዎችንም ሆነ ገንዘብ እንዲሁ፡፡ አንዲት ልጃገረድ ግን ለእንዲህ ዓይነት ወንድ ልጅ መሠጠትን የመሠለ ነገር የለም ምክንያቱም እሱ የሚፈልገው ይህንን ነውና

- አንቺ ሴት ልጅ ነሽ ኒና! እቃ አይደለሽም <<እንደ ሴት ክብርሽን ጠብቂ፡፡>> አንቺ የምትፈልጊውን ጠቃሚ ነገር እርሱ እንደሚፈልገው ታውቂያለሽ፡፡
- ለራስ የምታስቢ ራስ ወዳድ ነሽ ካለሽ አንቺም እንዲሁ በይው፡፡

አዳማ - አንቺ እኮ በባህር ውስጥ የምትገኚ ብቸኛ አሳ አይደለሽም! ማን እንደሆንሽ ታውቂያለሽ ?

አክስት - ነገር ግን አንድ ወንድ ልጅ ከልቡ ሲያፈቅር መጀመሪያ የሚያስደስተው ነገር ቢኖር የሚወዳት ሴት ራሷን እና ሰውነቷን ስታከብር ነው፡፡

አዳማ - ቆይ ኒና!

አክስት - ከመጀመሪያውኑ ነገሮችን ግልጽ ብታደርጊያቸውና መልሱ አይሆንም በማለት ምንም ጥርጣሬ እንዳይገባሽ፡፡ አንኚ ዝግጁ እስክትሆኚ ድረስ መልስሽ አይሆንም ነው፡፡ አሁን መሄድ ትችያለሽ፡፡

አክስት - መልካም ቀን ይሁንልሽ

*******